3.0/481/28

03 መጋቢት 2003

Ethiopian Revenues and Customs Authority

ለአ/አ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአ/አ የንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት /አዳማ/
ለሚሌ ቅ/ጽ/ቤት /ሚሌ/
ለባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት /ባህርዳር/
ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት /መቀሌ/
ለጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት /ጅጅጋ/
ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት /ድሬዳዋ/
ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/
ለሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት /ሞያሌ/
ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት /ሐዋሳ/
ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት /ጅማ/

ጉዳዩ፡- <u>የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ</u>

ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ጥር 127/2013 52/2003 ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ ስለሆነ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

02/07/03

ነቢዩ ሳሙኤል
ም/ዋና ዳይሬክተር
የኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለአዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለኦፐሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ
- ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ዘርፍ
- ለህግ ምክርና ማሻሻያ ቡድን

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

# ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎችን የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 127/2013

ወደ አገር ውስጥ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 68/3/ መሰረት ባለስልጣኑ የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታ እንደሚወስን የተደነገገ በመሆኑ፣

ከቀረጥና ታክስ ነፃ የገባው ተሽከርካሪ ሲጠፋ፣ በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ ውድመት ሲያጋጥመው ግለፅና ወጥ የሆነ የቀረጥና ታክስ አሰራር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 112/2/ መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎችን የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታን ለመወሰ የወጣ መመሪያ ቁጥር 127/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጉም

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-

1. *"ባለመብት"* ማለት በህግ ወይም ከመንግስት ጋር በተደረገ ስምምነት ተሽከርካሪን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ሆኖ ለማስገባት የተፈቀደለት ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ያለው ማናቸውም ሰው ነው።

2. *"ከፍተኛ ጉዳት"* ማለት የደረሰው አደጋ ተሽከርካሪው የነበረውን ባህሪ እንዲቀይርና ከተሰራበት ዓላማ አንፃር ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት የማይችል እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑ በጉዳት ገማች ባለሙያ የተረጋገጠ ወይም የማስጠገኛ ወጪው ኢኮኖሚያዊ ባለመሆኑ እንደወደመ እንዲቆጠር የሚያደርግ ጉዳት ሲሆን የተሽከርካሪውን መጥፋት ያካትታል።

3. *"ተሽከርካሪ"* ማለት በሞተር ሀይል በመንገድ የሚንቀሳቀስ የሰው ወይም/እና የጭነት ማጓጓዣ ሲሆን እንደ ትራክተር፣ ዶዘር፣ ኤክስካቬተር እና የመሳሰሉትን ሌሎች ማሽነሪዎችን ይጨምራል።

4. *"የአገልግሎት ቅናሽ"* ማለት ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ጉዳት እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ እንደየአገባቡ በየዓመቱ አስር በመቶ ወይም አስራ ሁለት በመቶ ከተሽከርካሪው ቀረጥና ታክስ ማቀናነስ ነው።

5. *"የአገልግሎት ዘመን"* ማለት ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እንደየ አግባቡ አሥር አመት ወይም አስራ ሁለት አመት እስከሚሞላው ድረስ ያለው ጊዜ ነው።

6. **"የአደጋ ጉዳት ቅናሽ"** ማለት የመድን ሽፋን ባልተገባላቸው ተሽከርካሪዎች ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት የጉዳት መጠኑ ከተሽከርካሪው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የሚደረግ ተቀናሽ ነው።

7. *"የጉዳት ገማች ባለሙያ"* ማለት በተሽከርካሪዎች ላይ የደረሰን ጉዳት ለመገመት አግባብነት ካለው የመንግሥት አካል ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው።

8. "የስራ ሂደት" ማለት በባለስልጣኑ ቅ/ፅ/ቤት የሚገኘውን በመንግስት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀምን ወይም በቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የሚከታተል አካል ነው፡፡

9. "የመድን ሰጪ" ማለት በአንድ ወይም በብዙ የተመደበውን የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ (ፕሪምዬም) ተቀብሎ በውሉ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የገባ ሰው ነው፡፡

10. *"ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡*

11. *"አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡*

12. ሌሎች በዚህ መመሪያ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

## 3. *<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>*

1. ይህ መመሪያ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ሆነው ወደ ሀገር ውስጥ በገቡና ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባቸው፣በጠፉ፣በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ በወደሙ ተሽከርካሪዎች ላይ እና ከተሽከርካሪው ጋር በተያያዘ መብትና ግዴታ በተጣለባቸው አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. በንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የገባው ተሽከርካሪ የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰ ከሆነ ይህ መመሪያ ተፈፃሚ አይሆንበትም፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# *<u>የመድን ሽፋን ስለተገባላቸው ተሽከርካሪዎች</u>*

## 4. *<u>የማሳወቅ ግዴታ</u>*

1. የመድን ሰጪው በቀረጥ ነፃ የገባው ተሽከርካሪ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት፣የጠፋ፣ በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ መውደሙ ከባለመብቱ ሪፓርት የደረሰው

እንደሆነ ወዲያውኑ ለባለስለጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመንግሥት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ማሳወቅ አለበት፡፡

2. የቀረጥ ነፃ ባለመብቱ መድን ሲገባ ያቀረባቸውን ሰነዶች እና ከመድን ሰጪው ጋር የተደረገውን ውል ከመመሪያው ጋር አባሪ ከተደረገው ቅፅ 1 ጋር በማያያዝ የመድህን ሰጪው ለባለሥልጣኑ ቅ/ፅ/ቤት በመንግሥት ለተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ተሽከርካሪው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት፣የጠፋ፣በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ መውደሙ ሪፖርት በተደረገ በ15 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

## 5. የመድን ሰጪው ሌሎች ግዴታዎች

1. ማንኛውም መድን ሰጪ ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ለገባ ተሽከርካሪ የመደን ዋስትና ሲሰጥ የተገባው ዋስትና ለተሽከርካሪው ቀረጥና ታክስ ጭምር መሆኑን ማረጋገጥ እና ይህንኑ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. የመድን ድርጅቱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰውን ሳያደርግ ቀርቶ ተሽከርካሪው ከፍተኛ ጉዳት ቢያጋጥመው የመድህን ድርጅቱ ለተሽከርካሪው ቀረጥና ታክስ አከፋፈል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. የመድን ድርጅቱ ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰበት ተሽከርካሪ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 15(1) መሰረት ተሰልቶ እንዳወቀ ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

## 6. የባለመብቱ ግዴታ

በባለመብቱ በቀረጥ ነፃ የገባው እና የመደን ሽፋል የተገባለት ተሽከርካሪ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት፣የጠፋ፣ በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ መውደሙ እንዳወቀ ለባለስለጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመንግሥት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 7. የቅርንጫፍ ፅ/ቤት ኃላፊነት

የሥራ ሂደቱ ከመደን ሰጪው ስለተሸከርካሪው ከፍተኛ ጉዳት የቀረበለትን ማስረጃ ካረጋገጠ በኋላ ተሸከርካሪው ላይ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ ወይም ክፍያ እንዲከፍል በማድረግ ተሸከርካሪው ከቀረጥና ታክስ ግዴታ ነፃ መሆኑን የሚገልፅ ወይም የሚያረጋግጥ ቀረጥ የተከፈለበት ዲክላራሲዮን እና ደረሰኝ በባለመብቱ ስም አትሞ ይሰጣል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመድን ሽፋን ያልተገባላቸው ተሸከርካሪዎች

## 8. የማሳወቅ ግዴታ

1. ከቀረጥ ነፃ የገባ ተሸከርካሪ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት፣የጠፋ፣በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉበሙሉ የወደመ እንደሆነ የቀረጥ ነፃ ባለመብቱ ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ሪፖርት በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ተሸከርካሪው ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚያሳይ የጉዳት ገማች ባለሙያ ሪፖርትና በመመሪያው አባሪ ከተደረገው ቅጽ 2 ወይም ቅፅ 3 ጋር በማያያዝ ለባለሥልጣኑ የቅ/ፅ/ቤት በመንግሥት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ማቅረብ አለበት፡፡

## 9. የቅርንጫፍ ፅ/ቤት ኃላፊነት

1. የስራ ሂደቱ የቀረበለትን በመመርመር የተሸከርካሪው የቅሪት አካል በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር እንዲውል ሲያዝ ባለመብቱ በ20 ቀናት ውስጥ ጉዳት የደረሰበትን ተሸከርካሪ በአካባቢው ለሚገኘው የጉምሩክ ጣቢያ ማስረከብ አለበት፡፡ሆኖም ግን

በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ማድረግ ያልቻለበት ምክንያት በስራ ሂደቱ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ተጨማሪ አስር የስራ ቀናት ሊሰጠው ይችላል።

2. የሥራ ሂደቱ ተሽከርካሪው ለባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ገቢ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በአዋጁ ዕቃ አወጋገድን አስመልክቶ በተደነገገው መሠረት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ እንዲሸጥ እና የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያደረጋል።

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ቢኖርም ባለመብቱ በተሽከርካሪው ቅሬት አካል ላይ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል ቅሪቱን ለመውሰድ የፈለገ እንደሆነ ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ ሊረከብ ይችላል።

## 10. ቀረጥና ታክስ ቀሪ ስለሚደረግባቸው ሁኔታዎች

1. ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ የገባ ተሽከርካሪ የጠፋ ወይም በአደጋ ምክንያት ሙሉ በሙሉ የወደመ እና ቅሪት የሌለው እንደሆነ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 መሰረት የቀረበለት ማስረጃ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ቀረጥና ታክሱ በሙሉ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል።

2. ሆኖም ከፍተኛ ጉዳት የደረሰው በሌላ ሶስተኛ ወገን በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14(2) የተገለፀው ተፈፃሚ ይሆናል።

## 11. ለጠፋ ፣በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ ለወደመ ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ ቀሪ ለማድረግ የሚቀርብ ማስረጃ

1. ተሽከርካሪው በመጥፋቱ ምክንያት ባለሥልጣኑ ቀረጥና ታክሱን በሙሉ እንዲቀር ሊያደርግ የሚችለው ከዚህ በታች የተመለከቱት ማስረጃዎች ሲቀርቡ ነው፡-

   ሀ. ተሽከርካሪው የጠፋ ስለመሆኑ ባለመብቱ በዕለቱ ለፖሊስ ያመለከተበት ሰነድ፣

   ለ. ለትራፊክ ፖሊስ እና/ወይም ለወንጀል መርማሪው ተሽከርካሪው መጥፋቱን አስመልክቶ ፍለጋ ወይም ምርመራ እንዲካሄድ የተመራበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

ሐ. ስለተሽከርካሪው መጥፋት ለመንገድ ትራንስፓርት ያሳወቀበት እና ሊብሬው እንዲሰረዝ ተጠይቆ ተቀባይነት ያገኘበት እንዲሁም ሊብሬው መመለሱን የሚያስረዳ ማስረጃ፣

መ. ለተሽከርካሪው መጥፋት ምክንያት ወይም ኃላፊ የሆነ ሰው ወይም አካል አለመኖሩ በፓሊስ የተረጋገጠ መሆኑን የሚያሳይ ደብዳቤ፣

ሠ. ተሽከርካሪ ተፈልጐ ሊገኝ ያልቻለ መሆኑን ፓሊስ ያሳወቀበት ደብዳቤ ከተሽከርካሪው ሙሉ ዶክመንት ጋር ተያይዞ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ በመንግሥት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪው በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ በመውደሙ ምክንያት ባለሥልጣኑ ቀረጥና ታክሱን በሙሉ እንዲቀር ሊያደርግ የሚችለው የሚከተሉት ማስረጃዎች ሲቀርቡ ነው፡-

ሀ. ተሽከርካሪው ሙሉ በሙሉ መቃጠሉን ወይም በአደጋ መውደሙን የሚያረጋግጥ የፓሊስ ወይም የትራፊክ ፓሊስ ማስረጃ፣

ለ. ከቃጠሎው ወይም ከአደጋው የተረፈ ቅሪት ቢኖርም ቀረጥና ታክሱን ለመክፈል ከአሥር ፐርሰንት በላይ ሊሸፍን የማይችል መሆኑን ወይም በአደጋ የተጐዳውን ቅሪት ማንሳት ቅሪቱ ከሚያወጣው ዋጋ በላይ መሆኑ በጉዳት ገማች ባለሙያ የተረጋገጠበት ማስረጃ፣

ሐ. የተሽከርካሪው ሊብሬ ወይም የሰሌዳ ቁጥር በመንገድ ትራንስፓርት እንዲሠረዝ የተጠየቀበት ማስረጃ፣

መ. ተሽከርካሪው በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ እንዲወድም ምክንያት ወይም ኃላፊ የሆነ ሦስተኛ ወገን አለመኖሩን በፓሊስ የተረጋገጠበት ደብዳቤ ለስራ ሂደቱ ያቀርባል፡፡

## 12. የቅርንጫፍ ፅ/ቤት ኃለፊነት

1. ለጠፋ ተሽከርካሪ ሲሆን የሥራ ሂደቱ የቀረበውን ማስረጃ ከተሽከርካሪው የአገልግሎት ዘመን ጋር በማገናዘብ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ቀረጥና ታክሱን በሙሉ እንዲቀር እና ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ እንዲሰረዝ ለማድረግ የውሳኔ ሀሳቡን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

2. በሥራ ሂደቱ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በሥራ አስኪያጁ ሲፀድቅ ቀረጥና ታክሱ በሙሉ እንዲቀርና ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ እንዲሰረዝ ውሳኔውን ለቅ/ጽ/ቤቱ የቀረጥ አሰባሰብ የሥራ ሂደት በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

3. በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ ለወደመ ተሽከርካሪ ሲሆን የሥራ ሂደቱ የቀረበለትን ማስረጃ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ቀረጥና ታክሱ በሙሉ እንዲቀር እና ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ እንዲሰረዝ የውሳኔ ሀሳቡን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

4. የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ሥራ አስኪያጁ ያፀደቀው እንደሆነ ቀረጥና ታክሱ በሙሉ እንዲቀር እና ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ እንዲሰረዝ ውሳኔውን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የቀረጥ አሰባሰብ የሥራ ሂደት በደብዳቤ ይገልፃል፡፡

## 13. የተሽከርካሪው መጥፋት፣መቃጠል ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ መውደም ተቀባይነት ሲያጣ

1. በአንቀፅ 11/1/ እና /2/ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ያልተሟሉ እና የቀረበው ማስረጃ በመንግስት አካል ሳይረጋገጥ ሲቀር በመንግሥት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት እንዳላገኘ እና ቀረጥናታክስ ቀሪ እንደማይሆን ለባለመብቱ በ20 ቀን ውስጥ ያሳውቃል፡፡

2. የሥራ ሂደቱም የቅ/ጽ/ቤቱ የቀረጥ አሰባሰብ የሥራ ሂደት ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ሲገባ የነበረውን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መነሻ በማድረግ ቀረጥና ታክሱ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ባለመብቱ ባለዕዳ ለሆነበት ቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታና ጊዜ በቅ/ፅ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 14. *ኃላፊ ስለመሆን*

1. ተሽከርካሪው እንዲጠፋ፣በአደጋ ወይም በቃጠሎ እንዲወድም ምክንያት የሚሆን ሰው ተሽከርካሪው ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ባለው ቀሪ የአገልግሎት ዘመን ላይ ቀረጥና ታክሱ ተሰልቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
2. በአንቀፅ 11/1/ እና /2/ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ቀረጥና ታክሱ በሙሉ እንዲቀር ሊያደርግ የሚችለው ባለመብቱ ለደረሰው ጉዳት ከሶስተኛ ወገን ካሳ ያልተቀበለ ወይም መቀበል የሚችልበት ዕድል የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡
3. ባለመብቱ ለተሽከርካሪው መጥፋት፣በአደጋ ወይም በቃጠሎ መውደም ምክንያት ከሆነው ሰው ሆን ብሎ ካሳ የመጠየቅ መብቱን የተወ እንደሆነ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 15. የቀረጥና ታክስ ስሌት

1. የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ የቀረጥና ታክስ ስሌት በተመለከተ ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ሲገባ ይከፈል የነበረውን ቀረጥናታክስ መሰረት በማድረግ ተሽከርካሪው ጉዳት እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ በየዓመቱ የአገልግሎት ቅናሽ በማድረግ ቀሪውን ቀረጥና ታክስ መድን ሰጪው እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

2. የመድን ሽፋን ያልተገባለት ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ የሚሰላው ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ሲገባ የነበረው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን መነሻ በማድረግ ተሽከርካሪው ጉዳት እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ በየዓመቱ የአገልግሎት ቅናሽ እንደያግባቡ 10% ወይም 12% በመቀነስ ከሚገኘው ዋጋ ላይ የጉዳት ገማች ባለሙያ የሚሰጠው የጉዳት መጠን ተቀንሶ የሚገኘው ውጤት አሁን ባለው የውጭ ምንዛሪ ተባዝቶ ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ሲገባ ለነበረው የውጭ ምንዛሪ ተካፍሎ የሚገኘው ውጤት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ይሆናል፡፡

3. በተራ ቁጥር (2) በተጠቀሰው መሰረት የተሽከርካሪው ቅሪት ሲሸጥ ከቀረጥና ታክሱ ዋጋ በላይ ሆኖ ሲገኝ የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ከቀረጥና ታክሱ የተረፈውን ገንዘብ ለባለመብቱ እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

## 16. ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ገቢ አለማድረግ

በአንቀፅ 9(1) መሰረት ባለመብቱ ተሽከርካሪውን ለባለስልጣኑ እንዲያስረክብ የተወሰነበትን ውሳኔ በመተላለፍ ተሽከርካሪውን በአቅራቢያው ለሚገኘው የጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት ወይም ጣቢያ ገቢ ያላደረገ እንደሆነ ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ሲገባ የነበረውን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን መሰረት በማድረግ ቀረጥና ታክሱ ተሰልቶ ባለመብቱ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 17. ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ከመዝገብ ላይ ስለመሰረዝ

### ሀ. የመድን ሽፋን የተገባላቸው ተሽከርካሪዎች

1. ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰበት ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክሱን የሰበሰበው የሥራ ሂደት ወይም የጉምሩክ ጣቢያ በሳምንቱ መጨረሻ ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰበት ተሽከርካሪ እንዲሰረዝ የዲክላራሲዮኑን ድርሻ ኮፒ ለሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት በመንግሥት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

2. የቅ/ጽ/ቤቱ በመንግሥት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ቀረጥና ታክስ ለመሰብሰቡ ከቀረጥ ሰብሳቢ የሥራ ሂደት ወይም የጉምሩክ ጣቢያ የተላከለትን የዲክላራሲዮን ኮፒ ድርሻ መሰረት በማድረግ ቀደም ሲል ከመድን ድርጅት ጥያቄ ሲቀርብ ከመዘገበው መረጃ ጋር አስታርቆ ተሽከርካሪውን ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ ይሰርዛል፡፡

## ለ. መድን ያልተገባላቸው ተሽከርካሪዎች

1. መድን ያልተገባላቸው ተሽከርካሪዎች በተመለከተ ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ የሚሰረዙት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8/1/ እና 9/1/ መሠረት ባለመብቱ ለሚመለከተው የሥራ ሂደት ሲያሳውቅ እና ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ለባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ገቢ እንዲሆን ተወስኖ ገቢ ሲያደርግ ነው፡፡
2. በመመሪያው አንቀፅ 11 መሠረት ቀረጥና ታክሱ ቀሪ እንዲሆን ውሳኔ ያገኙትን የቀረጥ ነፃ ጉዳዮች ከቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ደብዳቤው ሲደርሰው የሥራ ሂደቱ ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ ይሰርዛል፡፡

## 18. የአገልግሎት ዘመኑ ስላለፈ ተሽከርካሪ

የመድህን ሽፋን የተገባለትም ሆነ ያልተገባለት እና አስር አመት ወይም አስራ ሁለት አመት ያለፈው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት፣ የጠፋ፣በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ የወደመ ተሽከርካሪ ለመስተንግዶ በሚቀርብበት ጊዜ ለባለመብቱ በዜሮ የማስከፈያ ዋጋ ዲክላራሲዮን ታትሞ በ c.p.c 488 ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡

## 19. በቀረጥ ነፃ ገብቶ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ አላግባብ መገልገል

በቀረጥ ነፃ ገብቶ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ለሦሥተኛ ወገን አስተላልፎ የተገኘ ሰው በአዋጁ ድንጋጌ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 20. ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ አለማሳወቅ

መድን ሰጪው ወይም የቀረጥ ነፃ ባለመብቱ በአንቀፅ 4/1/ እና 8/1/ ላይ የተገለፀውን ድንጋጌ በመተላለፍ ተሽከርካሪው መጥፋቱን ወይም ጉዳት መድረሱን፣መቃጠሉን ወይም ሙሉ በሙሉ በአደጋ መውደሙን ወዲያውኑ ያላሳወቀ እንደሆነ ተሽከርካሪው ወደ አገር ውስጥ ሲገባ የነበረውን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ቀረጥና ታክሱን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 21. ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች ምትክ ስለማስገባት

1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም የኢንቨስትመንት ቢሮ ከቀረጥ ነፃ የገባው ተሽከርካሪ ላይ በደረሰው ከፍተኛ ጉዳት፣መጥፋት፣በቃጠሎ ወይም በአደጋ ሙሉ በሙሉ በመውደሙ ምክንያት ተሽከርካሪ በምትክነት እንዲገባ ሲፈቅድ የቀረጥ ነፃ ባለመብቱ ተሽከርካሪው ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ መሠረዙን የሚያሳይ ማስረጃ ከተሰጠው ፈቃድ ጋር በማያያዝ ለባለሥልጣኑ ቅ/ፅ/ቤት በመንግስት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የቅ/ፅ/ቤቱ በመንግስት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት የቀረበውን ማስረጃ ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ጋር በማመሳከር ተሽከርካሪው እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 22. ቁጥጥር ስለማድረግ እና መዛግብትን የመያዝ ግዴታዎች

1. የባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጁ በተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት መሠረት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባቸው የቀረጥ ነፃ ተሽከርካሪዎች ላይ የመድን ሽፋን አከፋፈልና አወጋገድ ወዘተ በተመለከተ በመድን ድርጅቶች ያሉ መዛግብትን በማስቀረብ ሆነ በአካል በመገኘት ሊመረምር ይችላል፡፡

2. በቀረጥ ነፃ ለገቡ ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን የሚሰጡ የመድን ድርጅቶች ባለመብቱ ለተሽከርካሪው የመድን ሽፋን ከገዛበት ጊዜ ጀምሮ ቀረጥና ታክሱ

በክፊልም ባይክፊልም ተሽከርካሪውን የሚመለከቱ ሙሉ ዶክመንቶች ስአሥር ዓመታት የማቆየት በአዋጁ የተጣለው ግዴታ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 23. መረጃ ስለመስጠት

የቀረጥ ነፃ ባለመብቱ በተሽከርካሪው ላይ የሚፈለገውን የቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎችን በተመለከተ ማስረጃ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የባለስልጣኑ ቅ/ፅ/ቤት በመንግስት የተሰጡ መብቶች አፈፃፀም የሥራ ሂደት ተገቢው ማስረጃ እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡

## 24. ቅሬታ ስለማቅረብ

የቀረጥ ነፃ ባለመብቱ ወይም መድን ሰጪው በዚህ መመሪያ መሰረት በቅ/ፅ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ውሳኔው በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታውን በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 25. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተጀምሮ እልባት ያላገኘ መድህን የተገባላትም ሆነ ያልተገባለት ተሽከርካሪ ጉዳይ በዚህ መመሪያ ሊስተናገድ ይችላል፡፡

## 26. የተሻሩ መመሪያዎች

1. ከቀረጥ ነፃ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ተሽከርካሪ መኪናዎች ባሉበት ሁኔታ ወደ ሶስተኛ ወገን ሲተላለፉ የቀረጥና ታክስ አከፋፈልን ለመወሰን በቁጥር ዘ60/በ3/05 በቀን 17/4/98 የወጣው የአፈፃፀም መመሪያ፣
2. ከኦፕሬሽን ዘርፍ በደብዳቤ ቁጥር Do4/54/72/6 በቀን 24/07/2001 ዓ.ም የተላለፈ መመሪያ ተሽሯል፡፡

3. እንዲሁም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አሰራርና ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 27. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ነቢይ ሳሙኤል
ም/ዋና ዳይሬክተር
(የኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ)

አዲስ አበባ--2/7/------ቀን 2003 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር

ቅፅ 1 ቁጥር -----------

ቀን-------------

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በደረሰበት ከፍተኛ አደጋ / በመጥፋቱ / በመቃጠሉ / በአደጋ ሙሉ በሙሉ በመውደሙ ምክንያት የተገባለትን የመድን ሽፋን ክፍያ የሚፈፀምበትን ተሽከርካሪ ማሳወቅን ይመለከታል

የመድን ሽፋን ክፍያ የሚፈፀምበትን ተሽከርካሪ፡-

1. የፖሊሲ ቁጥር_______________________፣
2. የመድን ሽፋን የተገባበት ቀን _____________ ዓ.ም. _______________፣
3. የመድን ሽፋን የገባው ግለሰብ/ድርጅት ስም _______________________ፊርማ ___፣
4. የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ ፡-
   - 4.1 ዓይነት_______________________________________፣
   - 4.2 የሻንሲ ቁጥር_______________________________________፣
   - 4.3 የሞተር ቁጥር_______________________________________፣
   - 4.4 የሰሌዳ ቁጥር_______________________________________፣
   - 4.5 የሊብሬ ቁጥር_______________________________________፣
   - 4.6 ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የተመዘገበበት የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፡-
     - ቁጥር___________________________፣
     - ቀን___________________________፣
     - የተመዘገበበት ጉምሩክ ጣቢያ ስም_______________፣
5. ተሽከርካሪው ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የነበረው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ብር__________፣

ከላይ ዝርዝር ሁኔታው ለተጠቀሰው ከፍተኛ አደጋ ለደረሰበት /ለጠፉ / በቃጠሎ / በአደጋ ሙሉ በሙሉ ለወደመ ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን ክፍያ ለመፈፀም እና በባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚፈለገውን ቀረጥናታክስ ወይም ክፍያ በመክፈል ተሽከርካሪውን በውክልና መረከብ እንዲፈቀድልን ባለመብቱ መድህን ሲገባያቀረባቸውን ሰነዶችእና ከመድን ሰጪው ጋር የተደረገውን ውል ከዚህ ጋር በማያያዝ እንጠይቃለን።

አባሪ፡- ____________ ገጽ ሰነዶች

ቅፅ 2 ቁጥር -----------

ቀን--------------

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የመድን ሽፋን ያልተገባለትን ተሽከርካሪ የደረሰበትን ከፍተኛ ጉዳት ማሳወቅ ይመለከታል

1.ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ባለቤት ስም________________ ፊርማ________

2.ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ፡-

2.1 ዓይነት________________________________________ ፣

2.2 የሻንሲ ቁጥር________________________________________ ፣

2.3 የሞተር ቁጥር________________________________________ ፣

2.4 የሰሌዳ ቁጥር________________________________________ ፣

2.5 የሊብሮ ቁጥር________________________________________ ፣

2.6 ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የተመዘገበበት የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፡-

- ቁጥር________________________ ፣
- ቀን________________________ ፣
- የተመዘገበበት ጉምሩክ ጣቢያ ስም____________

2.7 ተሽከርካሪው ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የነበረው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ብር________ ________________________ ፣

ከላይ ዝርዝር ሁኔታው ለተጠቀሰው ከፍተኛ አደጋ ከደረሰበት ተሽከርካሪ ቅሬት አካል ላይ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ወይም እንዲሰበሰብ ለማድረግ የደረሰውን ከፍተኛ አደጋ የሚያሳይ የጉዳት ገማች ባለሙያ ሪፖርት በማያያዝ እንጠይቃለን፡፡

አባሪ፡- ____________ ገጽ ሰነዶች

ቅፅ 3 ቁጥር------------

ቀን-------------

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የጠፋ፣በቃጠሎ/በአደጋ ሙሉበሙሉየወደመ የመድህን ሽፋን ያልተገባለትን ተሽከርካሪ ስለማሳወቅ

1.የጠፋው፣በቃጠሎ/በአደጋ የወደመው ተሽከርካሪ ባለመብት ስም___________፣ ____ፊርማ _________፣

2.የጠፋው፣በቃጠሎ/በአደጋ የወደመው ተሽከርካሪ፣

2.1 ዓይነት__________________________፣

2.2 የሻንሲ ቁጥር__________________________፣

2.3 የሞተር ቁጥር__________________________፣

2.4 የሰሌዳ ቁጥር__________________________፣

2.5 የሊብሬ ቁጥር__________________________፣

2.6 ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የተመዘገበበት የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፡-

- ቁጥር______________________፣
- ቀን______________________፣
- የተመዘገበበት ጉምሩክ ጣቢያ ስም__________፣

2.7 ተሽከርካሪው ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የነበረው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ__________፣

ከላይ ዝርዝር ሁኔታው ለተገለፀው የጠፋ ፣ በቃጠሎ / በአደጋ ሙሉ በሙሉ የወደመውን ተሽከርካሪ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ተሽከርካሪው መጥፋቱን ወይም ሙሉ በሙሉ መውደሙንና ቅሪት አለመኖሩን ከቅፁ ጋራ የቀረበውን ማስረጃ ተመልክቶ የሚፈለገውን ቀረጥናታክስ እንዲነሳልኝና ተሽከርካሪው ከቀረጥ ነፃ መዝገብ ላይ እንዲሰረዝልኝ እጠይቃለሁ።

አባሪ፡- _____________ገጽ ሰነዶች